# የሲምካርድ ምዝገባ መመሪያ

# ማብራሪያ

## 1. መግቢያ

የሲም ካርድ ምዝገባን ማከናወን የሃገሪቱን ኢኮኖሚ እና ደህንነትን በመጠበቅ ረገድ ከፍተኛ የሆነ አስተዋጾ ያደርጋል። ምዝገባ ያልተከናወነባቸው ሲም ካርዶች በገበያ ላይ እንዲኖሩ መፍቀድ በሃገር ደህንነት ላይ ከፍተኛ የሆነ ስጋት የሚደቅን ሲሆን በተለይም ሰዎች አልታወቅም የሚል ስሜት ስለሚሰማቸው ሲም ካርዱን ተጠቅሞ ወንጀል ለመፈጸም ይነሳሳሉ።

ከዚህም ባለፈ ሞባይልን መሰረት ያደረገ የንግድ ግንኙነትን ለማከናወን የሲም ካርድ ምዝገባ ቅድመ መስፈርት በመሆኑ እና ይህን ተግባራዊ አለማድረግ የሀገሪቱን የዲጂታላይዜሽን ሁደት የሚጎዳ ይሆናል።

ይህን መሰረት በማድረግ ባለስልጣኑ የሲምካርድ ምዝገባ መመሪያ ያዘጋጀ ሲሆን ይህም ዘርፉን በአግባቡ ማስተዳደር የሚያስችል ድንጋጌዎች የያዘ እና ውጤታማ ስራን መስራት ያስችላል ተብሎ ይታመናል።

## 2. የመመሪያው የሕግ መሰረት

የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን በኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 አንቀጽ 6(2)፣ 51(2) እና 54(2) መሰረት የሲም ካርድ ምዝገባ መመሪያ ማውጣት እንደሚችል ተመልክቷል። በእነዚህ ድንጋጌዎች ላይ ባለስልጣኑ የኮሙኒኬሽን ፖሊሲን ተግባራዊ አንደሚያደርግ እና የሲም ካርድ ምዝገባን ለመወሰን፥ ለማስተዳደር፥ ለመቆጣጠር እና እያንዳንዱን የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር፤ ደንበኛን እና ሌሎች ተሳታፊ አካላት ለመቆጣጠር ብቸኛ ስልጣን እንዳለው ተገልጿል። ከዚህ በተጨማሪም ባለስልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 54 (2) መሠረት አዋጁን እና አዋጁን መሠረት አድርገው የወጡ ደንቦችን የማስፈጸሚያ መመሪያዎችን የማውጣት ስልጣን የተሰጠው ሲሆን እነዚህን የህግ ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## 3. የመመሪያው ዓላማ

ይህ መመሪያ የተለያዩ አላማዎችን ከግብ ለማድረስ የተዘጋጅ ሲሆን በዚህ ክፍል ዋና ዋና ሊባሉ የሚችሉ የመመሪያውን አላማዎች ተመልከተዋል፤-

- የሲም ካርድ ምዝገባን እና አጠቃላይ የአሰራር ስርሃት ግልጽ በሆነ መንገድ መምራት የሚስችል የህግ ማዕቀፍ ማበጀት፤
- ብሔራዊ የሲም ካርድ ደንበኞች መዝገብን መቆጣጠር፣ ማስተዳደር እና መምራት የሚያስችል የቁጥጥር ማዕቀፍ ማዘጋጀት፤
- የሲም ካርድ ምዝገባን በማከናወን የሃገሪቱን የኤሌክትሮኒክ ንግድ ሂደትን ማፋጠን ፤

## 4. የመመሪያው የዝግጅት ሂደት

የመመሪያው ዝግጅት ከአንድ አመት በላይ የወሰደ እና በርካታ ሂደቶችም ያለፈ ሲሆን ረቂቅ ህጉ ተጠናቅቆ እስከቀረበበት ድረስ የተከናወኑ አበይት ተግባራት ወይም ሂደቶች በሚከተለው መልኩ ተጠቃልሏል።

- **ጥናት ማካሄድ፡-** እስካሁን ድረስ በሃገሪቱ ውስጥ ሲም ካርድን በበቂ ሁኔታ የሚያስተዳደር የሲም ካርድ ምዝገባን የተመለከቱ ህግ አልነበረንም። በመሆኑም ዘርፉን መሰረት ያደረገ ህግ ለመቅረጽ ጥናቶች ማካሄድና በጥልቀት መረዳት የሚጠይቅ ነው። ይህንን ለማሳካት የሃገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ፣ በዘርፉ የዳበረ ልምድ ያላቸው የሃገራት ተሞክሮ እና የቴክኖሎጂ እድገት በተመለከተ ጥናት ተደርጎል። በዚህ ጥናት አማካኝነት በመመሪያ ውስጥ ሊካተቱ የሚገባቸው ድንጋጌዎች እና ዋና ዋና ቁም ነገሮች ተለይቷል።
- **ለረቂቅ ህጉ ዝግጅት ግብአት የሚሆኑ ሞዴል ህጎችና ተሞክሮዎች መምረጥ፡-** የቴሌኮም ዘርፍ ላይ አለም-አቀፍ ተቋማት ተሳታፊ በመሆናቸው ዘርፉን የሚያስተዳድረው ህግም አለምአቀፍ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ መዘጋጀት አለበት። ስለሆነም የህጉ ይዘት አለም አቀፍ ደረጃው የጠበቀ ይሆን ዘንድ ከሃገሪቱ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች አንጻር ተቀራራቢ የሆኑ ሃገራት ህጎች በሞዴልነት ተመርጠዋል።
- **ባለድርሻ አካላትን ማወያየት፡-** ረቂቅ መመሪያውን ለማዳበር የሚከተሉት ሶስት የውይይት መድረኮች ተዘጋጅተዋል፡-
    - የሃገር ውስጥ እንዲሁም አለማቀፍ የቴሌኮም ኦፕሬተሮችን፣ ከዘርፉ ጋር ግንኙነት ያላቸው የመንግስት እና የግል ባለደርሻ አካላትን፣ የሲቪክ ማህበረሰብን፣ ዘርፉ ላይ የሚሰሩ የህግ ባለሙያዎችን ፣ባለሃብቶችን ወዘተ ተሳታፊ ያደረገ የአንድ ወር የምክከር መድረክ ተዘጋጅቷል።

- ረቂቁን በባለስልጣኑ ዌብሳይት ላይ ለ20 ቀናት ለሕዝብ አሰተያየት ክፍት እንዲሆን ተደርጎ፤ ፍላጎቱ ካላቸው የሃገር ውስጥ እንዲሁም አለማቀፍ ተቋማት በቂ የሆነ ግባት ለመሰብሰብ ተችሏል።
- ባለድርሻ አካላት ያነሱት ነጥቦችን እና ባለስልጣኑ የሰጠውን ምላሽ በተመለከተ ሦስተኛ የምክክር መድረክ ተዘጋጅቷል። በዚህ መድረክ ላይ በተሳታፊዎች የተነሱ ነጥቦች ላይ ውይይት የተደረገ ሲሆን በመመሪያው ላይ ሊካተቱ የሚገቡ ተጨማሪ ግባቶች ተገኝተዋል።

## 5. በረቂቅ መመሪያው ላይ የተነሱ ነጥቦች እና የተወሰዱ እርምጃዎች

በረቂቅ መመሪያው ላይ የተለያዩ የሃገር ውስጥ እና የውጪ ሃገር ባለድርሻ አካላት ተሳታፊ የሆኑ ሲሆን በመድረኩ ላይ የተለያዩ ጥያቄዎች ተነስተዋል። ከነዚህም ውስጥ የሚከተሉት ዋና ዋና ናቸው።

- በአዋጁ የተሰጡ ስልጣኖች እንደተጠበቁ ሆነው በመግቢያ (preamble) ክፍል ላይ መመሪያውን ማውጣት ያስፈለገበት ዋና ምክንያቶች ተለይተው በአንድ ወይም ሁለት ፓራግራፍ ውስጥ እንዲካተት ቢደረግ፤
- የመመሪያው ዋና ርዕስ የውድድር መመሪያ ብቻ መባሉ ከሌሎች ሀገራዊ የውድድር ህጎች ርዕስ ጋር ሊያመሳስለው ስለሚችል የበለጠ ግልፅ ለማድረግ የቴሌኮመኒኬሽን አገልግሎት ውድድር መመሪያ በሚል ግልፅ ተደርጎ ቢስተካከል።
- የክፍል አንድ ርዕስ ዝርዝሮቹን በማስወጣት “ጠቅላላ” ብቻ በሚል እንዲስተካከል ቢደረግ፤
- በኮሚኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ አንቀጽ 2(22) እንዲሁም በረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 2 (17) ላይ ሲም ካርድ የሚለው ቃል የተተረጎመበት መንገድ የተለያየ ነው። በረቂቅ መመሪያው ላይ የቃሉ ትርጎሜ ሰፊ እና ሁሉን አካታች ሆኖ የቀረበ ሲሆን ይህም ለቃሉ ከቴክኖሎጂ ነጻ የሆነ ትርጎሜ በመስጠት ወደ ፊት በዘርፉ ሊመጡ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን ማካተት ያስችላል። ይሁን እንጂ በመመሪያው ላይ የተሰጠው ትርጉም ከአዋጁ በጣም የተለየ ነው። በመመሪያው ለማድረግ የተሞከረው በአዋጅ የተቀመጠን ቃል ማሻሻል ነው። ይህ ደግሞ ከህግ መርህ ጋር አብሮ የሚሄድ አይደለም። ሰለሆነም ለቃሉ በአዋጁ የተሰጠው ትርጎሜ በቂ ካልሆነ አዋጁን ነው ማሻሻል የሚያስፈልገው። አዋጁን በመመሪያ ለማሻሻል መሞከር ግን አዋጁን ያወጣውን አካል ስልጣን መጋፋት ነው።

- ሲምካርድ የሚለው ቃል  በአዋጁም ሆነ በረቂቅ መመሪያው ላይ በስፋት ጥቅም ላይ ውሏል። ይህ ቃል አንድን ቴክኖሎጂ ብቻ የሚያመለክት ሲሆን ወደ ፊት በዘርፉ ሊፈጠር የሚችል የቴክሎጂ ለውጥን ግንዛቤ ውስጥ የከተተ አይደለም።  ለምሳሌ ቨርቾል ሲሞች በቅረብ ስራ ላይ ይውላል ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን ለእነዚህ እና መሰል ቴከኖሎጂዎች ሲም ካርድ የሚለው ቃል ገላጭ አይደለም። ከዛ ይለቅ በደፈናዋ ሲም-ካርድ የሚለው ቃል ሲም በሚለው ቢተካ ከካርድ ውጪ ሊኖሩ የሚችሉ ሲሞችንም ማካተት ስለሚያስችለው የተሻለ ይሆናል።
- በረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 8 ላይ ሲም ካርድ ለማውጣት ከሚያስፈልጉ መስፈርቶች መካከል ህጋዊ የሆነ መታወቂያ ማቅረብ አንዱ ነው። ይህ አካሄድ አሁንም በስራ ላይ ያለ ሲሆን ለብዙ ክፍተቶች የተጋለጠ ነው። ህገ ወጥ መታወቂያዎችን በመጠቀም ብዙ ቁጥር ያለው ሲም ካርድ ከኦፕሬተር መጋዘን የሚወጣ ሲሆን እነዚህም ሲም ካርዶች ለተለያ ወንጀሎች መፈጸሚያ መሳሪያ ሆነው እያገለገሉ ነው።  በዋናነትም ኮል ተርሚኔሽን ወንጀል ተጠቃሽ ነው። ስለሆነም ይህን ሁኔታ ለመከላል ብሔራዊ መታወቂያ ካርድ ተግባራዊ ማድረግ አንዱ የመፍቴ አቅጣጫ ተደረጎ ከዚህ በፊት የተቀመጠ ሲሆን ይህን መሰረት ያደረገ ማሻሻያ በረቂቁ ላይ ቢደረግበት የተሻለ ነው።
- መመሪያውን ማሻሻል በተመለከተ ክፍል ላይ መመሪያው በማንኛውም ወቅት እንደሚሻሻል ተደንግጓል። ይህ ግን የባለፍቃዶችን ጥቅም ስለሚጎዳ ባለድርሻ አካላት ተሳታፊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ቢፈጠር።

ከላይ የተመለከቱት እና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎች ላይ ሰፊ ውይይት የተደረገ ሲሆን ባለስልጣኑም የሃገሪቱን ጥቅም እና የቴክኖሎጂውን መስፋፋት የሚኖረውን ፋይዳ ግንዛቤ ውስጥ በመክትት የሚከተሉት ውሳኔዎች ተወስነዋል፡-

- የመመሪያው ርዕስ ላይ የተነሳው ጥያቄ አግባብነት ስላለው ማሻሻያ ተደርጎበታል፤
- መግቢያው ላይ የተነሳው ጥያቄ አግባብነት ያለው በመሆኑ ማሻሻያ ተደርጓበታል።
- ክፍል አንድ  አወቃቀር ላይ የተነሳው ሐሳብ ተገቢነት ስላለው ማሻሻያ ተደርጎበታል፤
- ከሲም ካርድ ትርጎሜ ጋር ተያይዞ የተነሳው ነጥብ ተገቢነት ስላለው ትርጓሜ ማሻሻያ ተደርጎበታል፤

- ከብሔራዊ መታወቂያ ህግ ጋር ተያይዞ የተነሳው ነጥብ ተገቢነት ቢኖረውም መታወቂያውን የተመለከቱ ስራዎች ገና በሂደት ላይ የሚገኝ በመሆናቸው በዚህ ረቂቅ ውስጥ ማካተት አልተቻለም፡፡
- መመሪያውን ባለስልጣኑ በማንኛውም ወቅት እንደሚያሻሽለው የተመለከተው ንግግር የአገልግሎት ሰጪዎችን ፍላጎት ስለሚጎዳ ይሻሻል የሚለው ጥያቄ ተገቢነት ስላለው ማሻሻያ ተደርጎበታል። በዚህም መሰርት ባለሰልጣኑ መመሪያውን ከማሻሻሉ በፊት ከባለድርሻ አካላት ጋር በጉዳዩ ዙሪያ ውይይት ማድረግ እንደሚኖርበት ተመልክቷል፡፡

**6. ለውይይት የተሰራጨው ረቂቅ መመሪያ እና የመጨረሻ ሆኖ የወጣው መመሪያ**

- በማስታወቂያ በተሰራጨው መመሪያ ላይ ባለስልጣኑ መመሪያውን በማንኛውም ወቅት እንደሚያሻሽለው ተመልክቷ የነበረ ሲሆን በመጨረሻ ረቂቅ ላይ ግን ባለስልጣኑ መመሪያውን ሲያሻሽል ከባለድርሻ አካላት ጋር በጉዳዩ ዙሪያ ውይይት ማድረግ እንደሚኖርበት ተመልክቷል። ይህ የተደረገበት ዋና ምክንያት ባለስልጣኑ በየወቅቱ ባለድርሻ አካላትን ሳያሳትፍ ማሻሻያ የሚያደርግ ከሆነ የአገልግሎት ሰጪዎችን ፍላጎት/ጥቅም ይጎዳል ከሚል ሕሳቤ የተነሳ ሲሆን ይህም ከባለድርሻ አካላትም በኩል በስፋት ሲንጸባረቅ ነበር። ጥያቄው የአዋጁን መንፈስ ያገናዘበ እና ተገቢ በመሆኑ እንዲስተካከል ተደርጓል።
- በመመሪያው መግቢያ ላይ ለመመሪያው መሰረት የተደረጉ ድንጋጌዎች ብቻ ናቸው የተካተቱት። ለመመሪያው መውጣት ምክንያት የሆኑ ነጥቦች አልተካተቱም የሚል አስተያት ከባለደርሻ አካላት በኩል ቀርቧል። ስለሆነም የመመሪያው መግቢያ የመመሪያውን አስፈላጊነት አጉልቶ በሚያሳይ መልኩ በድጋሚ ይስተካካል የሚለው ሕሳቤ/ አስተያት ተገቢ በመሆኑ በዛ መልክ እንዲስተካከል ተደርጓል።
- ክፍል አንድ የተዋቀረበት መንገድ የሃገሪቱን የህግ አወቃቀር የተከተለ አይደለም የሚለውን ጥያቄ በመቀበል በሃገሪቱ የተለመዱ የህግ አወቃቀር ተፈጻሚ እንዲሆን ተደርጎል፤
- በመመሪያው ላይ ለሲም ካርድ የተሰጠው ትርጎሜ ከአወጁ ጋር ይጋጫል የሚለው ሀሳብ ተቀባይነት ስላገኝ፤ መመሪው በዚህ ረገድ እነዲስተካካል ተደርጓል፡፡